# የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

2015 መጋቢት ቅጽ 3 ቁጥር 3


## ዓለምአቀፍ ዕውቅናን ያተረፈው የሶልሬብልስ ጫማ አምራች ኩባንያ መሥራች ወ/ሮ ቤተልሔም ጥላሁን ከፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ጋር በአጋርነት ለመሥራት የሚስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈረረሙ።

የመግባቢያ ሰነዱን የተፈራረሙት ዛሬ መጋቢት 15 ቀን 2015 ዓ.ም በፐርፐዝብላክ ዋና መሥሪያ ቤት በመገኘት ሲሆን ፐርፐዝብላክ ኢ.ቲ.ኤች ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም የተሰኘው የበይነ መረብ መገበያያ ሥርዓት ላይ በድርጅታቸው የሚመረቱትን የተለያዩ ለምግብ ፍጆታና ለአልባሳት የሚውሉ ቁሳቁሶች ማቅረብ እንዲችሉ መሆኑን ወ/ሮ ቤተልሄም ጥላሁን ተናግረዋል።

ከ300 ብር ወርኀዊ ደሞዝ ክፍያ ተነሥተው በዓለም አቀፍ ገበያ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለውን በአፍሪካ የመጀመሪያ ዓለምአቀፍ ዝናን (brand) ያተረፈ ሶልሬብልስ የተሰኘ ጫማ ማምረቻ እና ሌሎች የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን በማቋቋም በዓለማችንም ሆነ በአህጉራችን እጅግ ተጽዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉ ጥቂት እንስት መካከል አንዷ የሆኑት ወ/ሮ ቤተልሔም ጥላሁን ከፐርፐዝብላክ ኢ.ቲ.ኤች ትሬዲንግ አክሲዮን ማኅበር ጋር በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

> “
>
> ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሸማቹን ከገበሬው ጋር በቀጥታ ለማገናኘት የሚያስችሉ ሥርዓቶችን በመንደፍ የግብርና ውጤቶችን፣ የግብርና ማቀነባበሪያ ምርቶችንና የኢንዱስትሪ ፍጆታዎችን ከአምራቹ በቀጥታ ወደ ሸማቹ ማኅበረሰብ በችርቻሮ ሱቆቹ አማካኝነት እና በከገበሬው የበይነ መረብ መገበያያ ሥርዓት እያከፋፈለ መሆኑን አንስተው አሁን ላይ ኩባንያው ተደራሽነቱን ከኢትዮጵያ ወደ መላው አፍሪካ ለማስፋት የሚያስችለውን ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም የተሰኘ አዲስ የበይነ መረብ መገበያያ ሥርዓት ተግባር ላይ ሊያውል መሆኑን የፐርፐዝብላክ ኢ.ቲ.ኤች ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ገልጸዋል።

በመሆኑም በኢትዮጵያ መሠረቱን አድርጎ ዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ከፍተኛ አቅርቦት ያለውን ጫማ ፋብሪካ መመስረት የቻሉት ወ/ሮ ቤተልሔም በአገራችን እና በመላው ጥቁር ማኅበረሰብ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ታላቅ ራዕይ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ከሚገኘው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ጋር በጋራ በመተባበር ሥራዎችን መሥራት ጠቀሜታው ላቅ ያለ መሆኑንም አክለው አንስተዋል።

ምስል በ ነብዩ ዳንኤል




> “
>
> ለሰው ልጅ ለመኖር መሠረታዊ ከሚባሉ ነገሮች መካከል ምግብ፣ መጠለያና ልብስ መሆናቸውን ያነሱት ወ/ሮ ቤተልሔም ጥላሁን ፐርፐዝብላክ ኢ.ቲ.ኤችም ግብርና ላይ በማተኮር የኑሮ ውድነትን ታሪክ ለማድረግና ዜጎች በዘላቂነት ለምግብነት የሚውሉ ፍጆታዎችን እንዲያገኙ ለማስቻል እየተተረ በመሆኑ ያላቸውን አድናቆት ገልጸዋል።

ኩባንያው ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም በተሰኘው የበይነ መረብ መገበያያ ሥርዓት ቀደም ሲል ፐርፐዝብላክ ከሚያከፋፍላቸው የግብርና እና ኢንዱስትሪ ፍጆታዎች ባለፈ እንደ ሶልሬብልስ ያሉ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን የፋብሪካ ውጤቶች እንዲሁም ኤሌክትሮኒክስ፣ ፈርኒቸር፣ የመዋቢያ እቃዎች፣ የሕፃናት፣ ሴቶችና ወንዶች አልባሳት፣ ኬሚካሎችና የግንባታ እቃዎች፣ መኪኖች፣ መድኃኒቶች፣ ማዳበሪያና ማሽነሪዎችን በቀላሉ እና ፈጣን በሆነ መንገድ መገበያየት የሚቻልበትን አሠራር ለመዘርጋት በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

ከወ/ሮ ቤተልሔም ጥላሁን ጋር የተደረገው ስምምነት ይህንኑ መሠረት ያደረገ መሆኑን በሌሎች የኩባንያው የሥራ መስኮች ላይ በጋራ መሥራት የሚያስችል መሆኑ ተነግሯል። በመርሐግብሩ ላይ ፐርፐዝብላክ ኢ.ቲ.ኤች ወ/ሮ ቤቴልሔም ጥላሁንን የክብር አምባሳደር አድርጎም ሾሟል።

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በፐርፐዝ ብላክ ኢትዮጵያ የቀረበለትን "የከገበሬው ታወር ሎን ፕሮዳክት" የአጋርነት ጥያቄ እንደመልካም አጋጣሚ እንደሚመለከተው አስታወቀ።

ባንኩ ይህን የገለጸው በፐርፐዝ ብላክ ኢትዮጵያ ለከገበሬው ታወር ግንባታ በሚውለው የአክሲዮን ሽያጭ ዙሪያ በአጋርነት ለመሥራት በጠራበት ስብሰባ ላይ ሲሆን በስብሰባውም ላይ የኩባንያው የሥራ ክፍል ኃላፊዎችና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋናው መስሪያ ቤት ጥሪ የተደረገላቸው የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።



**“ የTCTዝብላክ ኢቲ.ኤች አመሠራረት እና የተሰማራባቸውን ዘርፎች በሚመለከት ጠለቅ ያለ ማብራሪያ የሰጡት የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ፣ በአህጉርና በአገር አቀፍ ደረጃ በቁመትና በግዝፈት ቀዳሚ የሚሆነው “ከገበሬው ታወር” የተሰኘ ሕንጻ በ 60 ቢሊዮን ብር በጀት ሊገነባ መሆኑን ለእንግዶች በመግለጽ ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ የገንዘብ አያያዝ ሁኔታን በማሻሻል እንዲሁም እርዳታን ወደ ኢንቨስትመንት በመለወጥ ረኀብን መዋጋት የሚሉ መሠረታዊ ሐሳቦችን መነሻ ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።**

የሚገነባው ሕንጻ ኢኮኖሚያዊ አቅምን መገንባት ላይ ትኩረቱን ያደረገና ግዙፍ ትልም ያለው ፕሮጀክት መሆኑንም ጠቁመዋል።

አክለውም የሁለቱንም ድርጅቶች ለትርፍ መቋቋም እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ትልቅ የማበደር አቅም በማስታወስ ይህ የከገበሬው ታወር ሎን ፕሮዳክት ለገበሬዎች በተለይም ለዲያስፖራው ማኅበረሰብ ከሚያቀርበው አማራጭ በዘለለ ከፕሮጀክቱ ግዙፍነት አንጻር እጅግ ትርፋማ እንደሚያደርጋቸው ገልጸዋል።

የጥቁር ሕዝብን ታሪክ መለወጥ የሚቻለው በግዙፍ ፕሮጀክቶች ነው ብሎ የሚያምነው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከመደበኛና ፍራንቻይዝ የአክሲዮን ሽያጮች በተጨማሪ ከፍ ያለ መጠን ያለውን ገንዘብ ለማንቀሳቀስና ትርፍን ለመጨመር በማሰብ በሚገነባው ሆቴል፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ሱቆችና ቢሮዎችን ባሟላው በዚህ ግዙፍ ሕንጻ ግንባታ ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ አካላትን ይበልጥ ተጠቃሚ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በጋራ ለመሥራት ፍላጎት ያላቸው ኢንቨስተሮች ለሚገዙት ሼር ብድር ለማመቻቸት ማቀዱን አስታውቋል።

ባንኩን በመወከል ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምክትል ፕሬዝደንት አቶ መንግስቱ ለማ በበኩላቸው ፐርፐዝ ብላክ ኢትዮጵያ ከገበሬው ታወር ሎን ፕሮዳክት በማለት ለአጋርነት ያቀረበለትን ጥያቄ እንደመልካም አጋጣሚ እንደሚመለከቱት በመግለጽ ስለተሰጣቸው የተሳትፎ ዕድል ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

**TCTዝብላክ ኢቲኤች ትሬዲንግ አክሲዮን ማኅበር ለመገንባት ላቀደው ባለ 115 ወለል ከገበሬው ታወር ግንባታ አክሲዮን ሽያጭ ጨረታ ማዘጋጀቱን አስታወቀ**



**“ TCTዝብላክ ኢትዮጵያ ከገበሬው ታወር በሚል ስያሜ ለመገንባት ላቀደው ባለ 115 ወለል ሕንጻ ግንባታ አክሲዮኖችን እንደሚሸጥ ያስታወቀ ሲሆን አክሲዮኖቹን ለመሸጥ ጨረታ ማዘጋጀቱን ገልጿል።**

ለመላው የኢትዮጵያ ገበሬ ማመስገኛነት የሚቆመው ይህ ታሪካዊ ሕንጻ በ20 ሺ ካሬ ሜትር መሬት ላይ የሚያርፍ ሲሆን በውስጡም የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና መሥሪያ ቤትን ጨምሮ ቅንጡ የመኖሪያ አፓርትመንት፣ ቢሮዎችና ሱቆች፣ ሆቴል፣ መዝናኛና የተለያዩ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ በቂ የመኪና ማቆሚያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ግንባታዎችን የሚያካትት ይሆናል።

በአህጉርና በአገር አቀፍ ደረጃ  በግዙፍነት ቀዳሚ የሚሆነውን ይህንን ሕንጻ ለመገንባትም 60 ቢሊዮን ብር ካፒታል የሚጠይቅ ሲሆን ባለሃብቶች የ 35 እና የ 55 ሚሊዮን ብር አክሲዮን በመግዛት የግንባታው አካል ብሎም የቅንጡ መኖሪያ ቤት ባለቤት መሆን ይችላሉ።

ፕሮጀክቱ ከያዛቸው እጅግ አጓጊ እና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ካላቸው የኢንቨስትመንት ዕድሎች በተጨማሪ ለአንድ  ወር የሚቆይ ጨረታ በማዘጋጀት ከባንኮች ጋር በተያያዘ የረጅም ጊዜ የብድር ክፍያ አማራጭ ሒደቱን ቀላል የሚያደርግ አሥራር መዘርጋቱን የከገበሬው ታወር ሼር ሆልደር ሞዴል ፕሮጀክት አስተባባሪ ኮሚቴ አስታውቋል።

አከፋፈሉም በሦስት ደረጃዎች የተከፈለ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ ጨረታው በወጣ በአንድ ወር ውስጥ ሙሉ ገንዘቡን የሚከፍሉ ባለሃብቶች የሚስተናገዱበት ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ 25 በመቶውን ቀድሞ በመክፈል ቀሪውን 75 በመቶ በረጅም ጊዜ ብድር የሚከፍሉበት እንዲሁም በሦስተኛ ደረጃ በረጅም ጊዜ የባንክ ብድር የሚከፍሉበት አማራጭ ነው፡፡

ጨረታው ከሚያዚያ 1 ቀን 2015 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም የሚቆይ ሲሆን ግንቦት 3 ቀን 2015 ዓ.ም. ተጫራቾች እና ሕጋዊ ወኪሎች በተገኙበት በይፋ ይከፈታል። የጨረታው አሸናፊዎች ገንዘቡን በጨረታ ሰነዱ በተቀመጠው አካሄድ መሠረት ከግንቦት 3 እስከ ግንቦት 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ገቢ የሚያደርጉ ሲሆን ገቢ የተደረገው የጨረታ ገንዘብ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዝግ አካውንት ይቀመጣል፡፡

ኮሚቴው እንዳስታወቀው ለጨረታ አማራጭ የቀረቡት ባለአምስት መኝታ ፔንት ሀውስ፣ ባለ አራት መኝታ ቅንጡ አፓርትመንት፣ ቢሮዎች እና የንግድ ቤቶች/ ሱቆች ሲሆኑ ማንኛውም ተጫራች በማይመለስ አንድ ሺህ ብር የጨረታ ሰነድ በመግዛትና የሚከፍሉትን ገንዘብ አንድ በመቶ (1%) ሲፒኦ በማስያዝ መሳተፍ ይችላሉ።

**“ “በገዙት አክሲዮን ልክ የአንድ አክሲዮን ዋጋ በአንድ ወር ውስጥ ሦስት እጥፍ የሚጨምር በመሆኑም ቀድሞ አንድ መቶ ብር የነበረው  ወደ ሦስት መቶ 300 ብር በማደግ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናሉ።” ሲሉ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ኮሚቴው አባል ወ/ሪት ቤዛዬ ንጉሤ ያስረዳሉ።**

ሕንጻው ተገንብቶ ሲጠናቀቅም ጨረታው ላይ ለመሳተፍ በቅድሚያ ሙሉውን የከፈሉ ባለሃብቶች እንደከፈሉት ገንዘብ መጠን በተመዘገቡበት ዘርፍ የመረጡትን የመውሰድና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት ይችላሉ። በመጨረሻም የታሪካዊው ከገበሬው ታወር ባለአክሲዮን ለመሆን ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን ማኅበራት፣ ኩባንያዎች፣ የአገር ውስጥና የውጪ ኢንቨስተሮች በዕድሉ መሳተፍ ይችላሉ ተብሏል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የእርሻ ፈጠራ ክፍል አሠራርን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የዳሰሳ ጥናት እያካሄደ መሆኑን አስታወቀ።

በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በቅርቡ ተደራጅቶ ወደ ሥራ የገባው የእርሻ ፈጠራ ክፍል ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት የሚያስችለውን የዳሰሳ ጥናት እያካሄደ መሆኑን አስታውቋል።

ወቅትን ብቻ ጠብቆ የመዝራት፣ የመሰብሰብና ለገበያ የማቅረብ ሒደትን በማስቀረት የግብርናውን ዘርፍ በቴክኖሎጂ መደገፍ ድህነትን ድል ለማድረግ ዓይነተኛ የመፍትሔ መንገድ ነው ብሎ የሚያምነው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዘመናዊ የመስኖ ልማት፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያና ባጠቃላይ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲቻል በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል።

ይህንንም ውጥን እውን ለማድረግ የእርሻ ፈጠራ ክፍል በማቋቋም በዓመት ውስጥ በ365ቱም ቀናት እርሻዎችን በማልማት የተትረፈረፈ ምርትና ምርታማነት ለማስመዝገብ የሚችልበትን መንገድ ቀይሷል።

የእርሻ ፈጠራ ክፍሉ በተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነቱን ለይቶ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን በመቅረጽ አሠራሩን ይበልጥ ለማሳለጥ ብሎም በቂ መረጃ እና ስልታዊ የመነሻ ሐሳብ ለማግኘት በኩባንያው የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እንዲሁም መላው ሠራተኞች ላይ የሚደረግ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ላይ ይገኛል።

የዳሰሳ ጥናቱ በዋናነት ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በተሰማራባቸው ክልሎችና ከተሞች በመልማት ላይ ያሉ እርሻዎችን ይዞታ መጠን፣ የክላስተሮችን እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችን ብዛት እንዲሁም በዓይነትና በመጠን የተለዩ ለኩባንያው የእርሻ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ታሳቢ በማድረግ ነባራዊ ሁኔታን ለመረዳት የተዘጋጀ መጠይቅ የያዘ ሲሆን ኩባንያው ዓመቱን ሙሉ ከሁሉም የእርሻ ፕሮጀክቶች ምርት እንዲያጭድ ማስቻል ዋና ግቡ ነው።

ምስል በ ነብዩ ዳንኤል



“በሁሉም የእርሻ ፕሮጀክቶች ውስጥ ቴክኖሎጂና በጥናትና ምርምር የተገኙ የእርሻ ግብአቶች ተካተው እንዲተገበሩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የኩባንያውን የግብርና ሥራ ማዘመን የእርሻ ፈጠራ ክፍሉ ዋና ተግባር ” ነው ያሉት የእርሻ ፈጠራ ክፍል ዳይሬክተር ወ/ሮ ሙላቷ ወልዴ የኩባንያው ፕሮጀክቶች ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ በመገንዘብ፤ በመረጃ ተደግፎ የቴክኖሎጂ እና የእርሻ ግብአት ፍላጎቶችን ለመለየት ያስችላል። ብሎም በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሥራ ክፍሉ ሥራውን ለማከናወን እንዲቻል ይህንን መጠነኛ የዳሰሳ ጥናት ማድረግ አስገዳጅ ሆኖ አግኝተነዋል” ሲሉ የዳሰሳ ጥናቱን አስፈላጊነት ያስረዳሉ።

ዳይሬክተሯ አክለውም “የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የእርሻ ፈጠራ ክፍል ኩባንያው እየተገበራቸው ባሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለአጠቃቀም ቀላል የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ፣ አካባቢንና የሰውን ጤና የማያውኩ ተፈጥሯዊ የእርሻ ግብዓቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ምርትና አገልግሎቱ በጥራትና በመጠን በማሳደግ ላይ ትኩረቱን አድርጎ ይሠራል ብለዋል።

የዳሰሳ ጥናቱ ሲጠናቀቅም በውጤቱ መሠረት የሚቀመጡ አቅጣጫዎችን ተግባራዊ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን የሚያጠናክሩ አሠራሮችን ለማስተዋወቅና ለማበረታታት፣ እሴት ጨምሮ ወደ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ለመሥራት ትልቅ አቅም ይሆናል። በተጨማሪም በአለም አቀፍ ደረጃ በዘርፉ ተወዳዳሪ ለመሆን በፐርፐዝብላክ ውጤታማ የምርምርና የአገልግሎት ዘርፍ ክፍልን በማጠናከር ተጨባጭ ለውጦችን ለማግኘት ያስችላል ተብሏል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በጸረ-ረኀብ እንቅስቃሴ 50 በጎ ፈቃደኞችን አሰልጥኖ ወደ ሥራ ሊያስገባ መሆኑን አስታወቀ።

50 በጎ ፈቃደኞች በጸረ-ረኀብ እንቅስቃሴ ስር ሰልጥነው ወደ ሥራ ሊገቡ መሆኑን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ግሎባል ኤቨንት ማኔጂንግ ዳይሬክተር ወ/ት ፍሬሕይወት ጌታቸው አስታውቀዋል።




በጎፈቃደኞቹ የፐርፐዝ ብላክ 6 ሱቆችን ጨምሮ፣ በብሔራዊ ቲያትር፣ በኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት ኤጀንሲ (ወመዘክር) እንዲሁም ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ላይ በመንቀሳቀስ ለኩባንያው ጸረ-ረኀብ እንቅስቃሴ አባላትን የሚመዘግቡ ይሆናል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ከብሔራዊ ቲያትር፣ ከኢትዮጵያ ቤተ-መጻሕፍትና ቤተ-መዛግብት ኤጀንሲ (ወመዘክር)፣ ከኢትዮጵያ ስፖርትና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም ከሌሎች 7 ድርጅቶች ጋር እንደ ተቋም በጋራ ለመሥራት በስምምነት ሒደት ላይ ይገኛል።

ዋና አዘጋጅ፦ ሰላማዊት ደበበ
ሲኒየር ሪፖርተር፦ ጌታባለው ገ/ሐና
ሪፖርተር፦ ኤደን ደነቀ

## ለበለጠ መረጃ

ስንገተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ

+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222

7151

www.purposeblackethiopia.com